ሰኔ 8ቀን 2015ዓም(June 15, 2023)

# ለአማራ ሕዝብ ህልውና የትጥቅና የሰላማዊ መሠረታዊ የትግል ዘርፎች!

በዘመናት ተጋድሎ የተገነባው የኢትዮጵያ አንድነት፣ ከ1983ዓም ጀምሮ፣በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት በተገንጣዮቹ በሻዕቢያ፣በትህነግ እና በኦነግ፣በቀጣዮቹ ዓመታት ደግሞ በትህነግ፣በኦነግና በብአዴን በ33ዓመት ውሥጥ እንደእንቧይ ካብ የተናደውና የአማራው ዕልቂት ሥር የሰደደው፣ከፕሮፌሰር አሥራትና መሠሎቻቸው በሥተቀር፣ በአማራውና ኢትዮጵያዊ ነን በሚሉት የህብረተሰብ ክፍሎች ንቃተቢስነት ነው።

ትህነግ እና ኦነግም!"ሕዝባችን በአማራ፣በኦርቶዶክስ፣በኢትዮጵያና ሠንደቋ ሥለተጨቆነና ቅኝ ሥለተያዘ፣ ዓላማችን! ጠላትን (አማራን) ደምሥሰን የመገንጠልን ግብ እናሳካለን" ነው ።ኢትዮጵያን ቢገዙም ባይገዙም፣ይህንን ዓላማቸውን ሲያጠናቅቁ ምንጊዜም የመጨረሻ ግባቸው በቅድሚያ ኮንፌዴረሽን የሚል ማዘናጊያ በመፍጠር ቀስ በቀስ መገንጠል ነው።

ዛሬ እነዚህ ጠላቶች ከቀደመው በተለዬ በቀጥታ አማራን ከሥር ከመሠረቱ እንደሚነቅሉት፣ የተወሰኑት አማራዎች ተረድተው፣ግብ ግብ ቢገጥሙም፣ከባንዳውና ከሆድ አደሩ ባሻገር፣ያልነቃው አማራ የትዬ ሌሌ ነው።ይህ ሆድ ያደማል፣ልብ ያቆሥላል፣ያማል።ቢነገረውም ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ፣ከጠላት ለማምለጥ "እንደሠጎን አንገቱን አሸዋ ውስጥ ደፍቋል"።ፕሮፌሰር አሥራት እንዳሉት "አማራው ሲተኛ የሚበላው ጅብ ነው"።

ያም ሆነ ይህ አንፃራዊ ንቃት ባላቸው ወገኖቻችን ትግሉ ተጠናክሮና በሕዝባዊ ክንድ ጠላቶቹን የትህነግን ትግሬድርጅቶች እና የኦነግን ኦሮሞድርጅቶች ከእነመከላካያቸው፣ፌደራላቸውና ልዩ ኃይላቸው ጭምር ተጋፍጦ፣የወገናችንን ደህንነት ለማረጋገጥ አማራጭ የለሹን የትጥቅ ትግል ተያይዞታል።ነገር ግን ቀድሞ መዝመት በሚገባው በውስጥ ቀንደኛ ጠላቱ በሆነው በብአዴን ላይ አለመዝመቱ እያሥጠቃው እንደሆን የተረዳ አልመሰለኝምና አሁንም ሳይዘገይ ይወቅበት።

ቁልፉ ጥያቄ አማራው ህልውናውን ለማሥጠበቅ፣የፖለቲካ ዕውቀትና ንቃት ባላቸው ሠዎች የሚመራ፣"ብሔሬ አማራ ነው፣ክልሌና ሀገሬ ኢትዮጵያ ናት" የሚል በአንድ ሊያሠልፈው የሚያሥችል ዓላማና ግብ ያነገበ፣ጠንካራና ጥራት ያለው፣ከማንም ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መንገድ፣በቅድሚያ በህቡዕ፣ጉልበት ሲፈረጥም በገሀድ የሚታገል የርዕዩተ ዓለም ፖለቲካውን ከትጥቅ ጋር ያጣመረ ድርጅት በማቋቋም፣ የአማራ ሕዝባዊ ግንባሩንና ኃይሉን(ልዩ ኃይሉን፣ፋኖውን፣ሚሊሽያውን፣ፖሊሱን ፣ወዘተ) ወደአንድ አምጥቶ ለድርጅቱ የአማራ ጦር ማድረግ በማሥቻል ተገዳዳሪ ሆኖ መውጣት ነው።

ይህንን አቋም ሲይዝ ነው፣ የጠላቶቹን ግብ መዳረሻ የሆኑትን፣የዓላማ ማሥፈፀሚያ መሣሪያዎችን፣ሥርዓቱን:ህገመንግሥቱንና የዘር ፌደራሊዝሙን ከሥር ከመሠረቱ ከእነአሥፈፃሚዎቹ ነቅሎ፣ የራሱን ሥርዓት መትከል የሚችለው።

ቀኝም ነፈሰ ግራ ይህንን የወገኖቻችን ተጋድሎ በሙሉ ልብ ሊገፉበት የሚችሉት፣ አሥፈላጊ በሆነው መንገድ ሁሉ ማለትም በጉልበት፣በገንዘብ፣በትግል፣በፅሁፍ፣በሀሳብ፣በሞራልወዘተ ማገዝ፣ማደፋፈር፣ማጎልበትና መርዳት፣ሥንችል ነው።የራስን ድርሻ እየተወጡ ሌሎችንም ማበረታታት እጅግ አሥፈላጊ ነው።

እሥካዛሬ እንደምናውቀው፣ይህንን ሳናደርግ የጥቂቶችን ጥረት ብቻ እየተከታተሉ ተዓምር በመጠበቅ እነርሱ ታግለው ነፃ እንዲያወጡን አንጋጥጠን የምናይ ከሆነ፣ለጠላቶች ጊዜ ይገዛላቸዋል፣ለወገን ግን ጠብ የሚልለት ነገር የለም።ትግሉ ግቡን ሳይመታ ቢቀር፣እኛ ራሳችን

በጥልቀት ማሰብ የተሳነን መሆናችንን ተቀብለን ለተሻለ ተግባር ከመነሳት ይልቅ፣ይበልጥ ራሳችንን ለማዳከም ሙያ ብለነው ብስጭት፣ንዴት እና ትችት እንደረድራለን።

እንደሚታወቀው በጠላትነት ጎራ የተሠለፉብን፣የትህነግ ትግሬድርጅቶች፣የኦነግ ኦሮሞድርጅቶች እና ብአዴን ብቻ ሳይሆኑ የዓለም ታላላቅ ኃይላት ጭምር ናቸው። ትግሉ ዘራችንን ከመጥፋት ለመታደግ፣ ርሥታችንን እንዳናጣ ተሥፋፊዎችን ለማንበርከክ፣በአጠቃላይ የህልውና ትግል ከመሆኑም በላይ ከእንግዲህ ሥልጣን ለመጨበጥም እንደሆነ ከወዲሁ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል።እሥከዛሬ አማራ እየሞተ ሥልጣን ለበላተኞችና ለገዳዮቻችን ሲያሥረክብ ኑሯል።ከእንግዲህ እንዲህ ዓይነት ሞኝነት ያከትማል።

ይህን የትጥቅ ትግል በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ የሚቻለው፣የተወሰኑ ታጋዮች ብቻ እየቆሰሉና እየሞቱ ነፃ እንዲያወጡት ቆሞ መመልከት ሳይሆን፣ዛሬ ከሚታየው በላይ ሠፊ የሕዝብ መሠረት እንዲኖረው፣ሁሉም በትንንቁ ውስጥ መሳተፍ ሲችል ነው።

ከታሪክ እንደምንረዳው በማንኛውም አገርና በየትኛውም ጊዜ፣አንድ ሕዝብ መብቱን ለማስጠበቅ የሚችልበት መንገድ ሲያጣ፣የትግል ዘዴዎችን ራሱ መርጦ ለመብቱ ይታገላል እንጅ እጆቹን አጣምሮ አይቀመጥም። ለምሳሌ የማህታ ማጋንዲን ህንድ፣የኔልሰን ማንዴላን ደቡብ አፍሪካንና የማርቲን ሉተርን አሜሪካ መጥቀስ በቂ ነው።

ይህ <u>ትጥቅ ትግል</u>(violent resistance) <u>በሠላማዊ ትግል</u> (non-violent resistance) ካልታገዘ የድል ቀንን ከማራዘምም ባሻገር ብዙ መሥዋዕትነት ያሥከፍላል።ሥለዚህ ከትትቅ ትግል በተጨማሪ አብዛኛው ሕዝብ፣ <u>በሰላማዊ ሰልፍ፣በኢኮኖሚ ማዕቀብ፣ ጨቋኝ ሕጎችን ባለማክበር፣ወዘተ</u> ሊሳተፍ የሚችልበት ዘርፍ <u>የሰላማዊ የትግል ዘርፍ</u> ነው። በተለይ ይህ በሌሎች ሀገራት ተደርጎ ውጤት ያስገኘው <u>የኢኮኖሚ ማዕቀብ</u> የሰላማዊ ትግሉ አካል ከመሆኑም በላይ የትጥቅ ትግሉን በአያሌው ሥለሚያግዝ፣ይህ አልተሠራበትምና የአማራው ሕዝብ ተግባራዊ እንዲያደርገው ያሥፈልጋል።

ነቅተን፣ተደራጅተን ከታጠቅን፣በእነኚህ በሁለቱ የትጥቅ እና የሠላማዊ ጣምራ ትግል እየተገለገልን፣የተነጠቅነውን መብትና አገር በእጃችን ከማድረግም አልፈን ሥርዓቱን አሽቀንጥረን ጥለን፣የራሥን ሥርዓት በመትከል፣የመገንጠል ምኞታቸውንም ማክሸፍ ይቻላል።በዚህ መልክ ዘረኞችን ማሰቆም ካልተቻለ፣ እነርሱ የመገንጠል ዓላማቸውን ግብ ለማድረስ እኛን ሳይጨርሱ አይተኙም።

ከሁሉ በፊት ለዘራችን ከምንውልለት ውለታ ቀዳሚው ህልውናችንን ለማሥጠበቅ፣ራሳችንን በማንቃት፣<u>አንድ ፀረ የጠላት ሥርዓት ዓላማና ግብ</u> ለመታጠቅ ሥንችል ነው።ተግባራዊ የሚሆነው ለመወያዬት የመከባበር፣የመደማመጥ፣የመማማርና ለመንቃት የመቁረጥ፣ቅን ልቦና ሲኖረን ነው።

ለብዙ ዓመታት <u>አማራው ባለመንቃቱ</u> ወዳጅና ጠላቱን ለይቶ ማወቅ ሳይችል ኑሯል።ይህንንም ሁኔታ ተጠቅመው ትህነግ እና ኦነግ በዝብዘውታል፣ኢኮኖሚያቸውን ለማዳበር ተጠቅመውበታል።ለምሳሌ

**(1)** ከአማራውና "ኢትዮጵያ" ከሚለው ወገን የሚያገኙትን የኢኮኖሚ ጥቅም እንዳያጡና ንግዳቸው እንዳይዳከም በሁለት ምላስ እየተናገሩ፣ሁለት ገፅታ እያሳዩ፣በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የተለያዩ ከተማዎች፣በደጋፊዎቻቸው አማካይነት <u>ከምግብ ቤቶች፣ከዳንስ አዳራሾች፣ ከታክሲ እስከ ምርት ድርጅቶች፣ልዩ ልዩ የንግድ ሥራዎችን ከእንጀራና ጤፍ ጭምር እንደሚያካሂዱ ይታወቃል።ለሽፋን ያህል ግን ንብረትነታቸው የግለሰቦቹ እንደሆኑ አስመስለው፣የንግድ ድርጅቶቹን በግለሰቦች ስም</u> ያሥመዘግባሉ።እኛ ንቃተቢሶቹ!ገንዘባችንን እየከሰከስን፣ይበልጥ እያሥታጠቅናቸው እንዲገድሉን እያመቻቸን ዛሬ ላይ ደርሰናል።

**(2)** መንግሥቱ ኃይለማርያም ያደረሰውን ዕልቂት ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ከፊልም ላይብረሪ የሚገኙትን ፊልሞችና ቪዲዮኖች በመውሰድ ፣የአፅም ቁፋሮ ትርኢት በማከልና በማዘጋጀት እስከ

50የአሜሪካ ዶላር ለአማራውና "ኢትዮጵያ" ለሚለው ወገን እየሸጠ፣የትህነግን(ወያኔ) ፀረአማራ ፖሊሲ ሲያራምድበት ኑሯል፡ባለምንቃታችን ከኪሳችን የወጣው የራሳችን ገንዘብ ራሳችንን እያፈናቀለንና እየገደለን፣ እንዲኖር አድርገናል።

**(3)** ብዙዎቻችን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሚገኘው ህብረተሰባችን! "መዝናናት ያስፈልገኛል"በሚል ግብዝነት፣ኪሱን በጠላቶች ምግብ ቤቶች፣ክለብና ዳንስ መድረኮች በማራቆት ሲውረገረግ በማደሩ ራሳቸው ጠላቶቻችን እንዲታዘቡንና እንዲንቁን አሥችሏቸዋል። "ምግብ ቤቶችን፣የዳንስ ቦታዎችን ወዘተ በአጠቃላይ የንግድ ሥራዎችን ፣አማራጭ ሳታቀርቡ አትገልገሉ ትሉናላችሁ" በማለትም ሲያማርር ኑሯል።የቤርሚንግሃም ጥቁሮችም(የጥቁር አሜሪካኖች የሰላማዊ ትግል ዘዴዎች የሚለውን ከታች ተመልከት) ሌላ የአውቶቡስ ኩባንያ ካልተቋቋመ ባለው አገልግሎት ከመጠቀም አናቋርጥም ሊሉ በቻሉ ነበር።

አማራጭ ባለበት ሁኔታማ መሥዋዕትነት ሥለማይጠይቅ፣ትግልም አይኖርም። ትግል ያሰኘው እኮ መሥዋዕትነት ሥለሚጠይቅ ነው።

**(4)** ከቢራ አቅም እንኳን እነኚህ ዘር የተጠናወታቸው ቡድኖች የሌሎቹን እያዳከሙ፣የራሴ ነው የሚሏቸውን የቢራ ገበያ በብቸኝነት ሲቆጣጠሩት፣በለዘብተኝነት ቆሞ ማዬትን መረጥን።በኦሮሞውም እንዲሁ።

**(5)** ከአማራው እየተዘረፈ በሚሄድ ጥሬ ሀብት እየተሰናዳ ወደአማራው የሚጎርፈውን ከሹራብና ከጨርቃጨርቅ ምርት ጀምሮ ያለውን ከመጠዬፍ ይልቅ ሥንበዘበዝ ኑረናል።ዛሬም ቀጥሏል።

አማራው ከነቃ ግን፣

**(1)** እንደ እሥከዛሬው "የራሷ አርሮባት የሰው ታማስላለች ወይም የመንታ እናት ተጋልላ ሞተች"እንደሚባለው ሳይሆን፣ራሱ እየጠፋ ለሌሎች ማሰቡን አቁሞ፣ሁሉንም ነገር ከአማራው ጥቅም አንፃር በማዬት፣ለህልውናው መቆም ይችላል።

**(2)** ፀረ አማራ ኃይላትና ደጋፊዎቻቸው ከሚያካሂዷቸው የንግድ ሥራዎች ድጋፋችንን በመንፈግ የሸቀጥ፣ እና የአገልግሎቶች ፍላጎቶን፣በአጠቃላይ የንግድ ሥራዎችን ወደአማራው ጎራ ያዞርነው እንደሆነ ውጤቱ የላቀ ይሆናል። በአጠቃላይ አማራውከነቃ በትግሬና በኦሮሞ ሱቆች፣ ቡናቤቶች መገልገል ያቆማል። የራሱን የአማራውን ሱቆች፣ምግብ ቤቶችና መጠጥ ቤቶች ይመርጣል።እህሉንም ለእነዚህ ጠላቶቹ አይሸጥም።

**(3)** አነስተኛ ነው፣እዚህ ግባ የማይባል ነው ሳይል አማራው የራሱን ሀብት አሰባስቦ የራሱን ሕብረተሰብ ልማት ያግዝበታል።ከሌሎች የንግድ ተቋሞች የሚያርቀው ሀብት እነሱን ካዳከመ፣ይህን ሀብት በማሰባሰብና በአግባቡ በመምራት ራሱ የሚመራቸውና የሚቆጣጠራቸው የምርት ተቋሞችን ለማደራጀት ይቻላል።

**(4)** አማራው ከነቃ የትጥቅ ትግሉንም ቢሆን፣አማራው ከልጅ እሥከ ዐዋቂ ከሚጎዳበት አሁን ከአለባቸው ከጎጃም፣ከጎንደር፣ከወሎና ከሸዋ አካባቢዎች ጎትቶ በማውጣት፣ከአራቱ ክፍላተሀገር ውጭ ኦሮሞና ትግሬ በብዛት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች እንዲሆንና እነርሱ እንዲደቁ ያድረጋል።እንዲህ ሲቀምሱት ነው የአማራው ቁስል የሚሰማቸው እና በአለቆቻቸው ላይ የሚያምፁት።

በሰላማዊ ትግል ዘዴዎች ከተሳካላቸው አገሮች መካከል የአሜሪካንን በመዳሰስ ትምህርት እንውሰድ ! በቅድሚያ የጥቁር አሜሪካውያን መብት ተከራካሪ ማርቲን ሉተር ኪንግ ከተናገራቸው ቁምነገሮች ጥቂቶቹን እንሆ!

(1)"ከአሳለፍናቸው መራር የትግል ልምድ እንደምናውቀው፣ጨቋኞች በፈቃዳቸው ነፃነትን ለሚጨቁኗቸው አይሰጡም።የተገፋው ሕዝብ በአሥገዳጅነት ይጎናፀፈዋል እንጅ" ብሎ ነበር።

(2) “ሠላማዊ ትግል የፈሪዎች የትግል ዘዴ ነው የሚባለው አስተሳሰብ ሥህተት ነው”ይላል።

ወደኢትዮጵያችን ሥንመጣ ይህንን የሠላማዊ ትግል የጀግኖች ከማለት ይልቅ የፈሪዎች ነው የሚለው አባባል ሥህተት ሆኖ እናገኘዋለን።ይኸውም በትናንትናው በትህነግም ይሁን በዛሬው በኦነግ፣ተቃዋሚው ሠላማዊ ሰልፍ ሲጠራ፣ለመሸሸግ የሚሞክረው፣በገለልተኝነት ለመታዬት የሚጥረው፣በአሥታራቂነት ሽርጉድ የሚለው፣የዚሁ የፍርሀትና ቆርጦ ያለመነሳት ነፀብራቆች ናቸው።

(3)“የትግሉ ዓላማ የጨቋኙን ሥርዓት ጭቆና በሰላማዊ የትግል ዘዴ በመጋፈጥ፣ጨቋኙ ኃይል የተያያዘው የጭቆና ሥልት የማያዋጣውና ኢሰብዓዊ መሆኑን ራሱ እንዲረዳው ለማስቻል ነው”ይላል።

ይህ አስተሳሰብ በአብዛኛው የአሜሪካ ነጮችን ሥሜት ለመቀስቀስና ለትግሉ ድጋፋቸውን ለማትረፍ ታስቦ የተቀዬሰ ነበር።በኢትዮጵያ ሁኔታም ኦነግ የያዘው ፖሊሲ የማያዋጣው መሆኑን፣ኦሮሞዎችም የዘለቄታ ጥቅማቸው በኦነግ ፖሊሲ እየተበላሸ መሆኑንና እንደአሜሪካ መንግሥት ያሉት ደጋፊዎቹም ስህተታቸውን እንዲረዱ ሊያበቃቸው ይችላል።

(4)“የትግሉ ግፊት የሚያተኩረው በጨቋኙ ኃይል ላይ እንጅ፣በግለሰቦች ላይ አይደለም” ይላል።

ይህን ከአገራችን ሁኔታ ጋር አገናዝበን ብናዬው፣ትግላችን ቀደም ሲል ከትህነግ፣ዛሬ ደግሞ ከኦነግ የጥፋት ፖሊሲ ጋር እንጅ ከትግሬ ወይም ከኦሮሞ ግለሰቦች ጋር አይደለም።ሆኖም ትግሬዎችም ኦሮሞዎችም ሆኑ ሌሎች እያወቁ በትህነግ/በኦነግ ፖሊሲ አሥፈፃሚነት ከተሰለፉ ከአማራውም ሆነ ከሌላው ሕዝባዊ ቁጣ ሊያመልጡ አይገባም።

ዘረኛ ሕጎችን መጣስን ወይም አለማክበርን ማርቲን ሉተር ኪንግ ለምን እንደሚያበረታታ ሲናገር፣”ሁለት ዓይነት ሕጎች አሉ፣<u>ትክክለኛ(Just) እ</u>ና <u>ትክክለኛ ያልሆኑ(Unjust)</u>።<u>ትክክለኛ ሕጎችን </u>ማክበር ሕጋዊም፣የሞራል ግዴታም ሥለሆነ ትክክለኛ ሕጎች እንዲከበሩ በመቀስቀስ ግንባር ቀደም እሆናለሁ።በአንፃሩ <u>ትክክለኛ ያልሆኑ</u> ሕጎችን አለማክበር የሞራል ግዴታ ነው”ይላል።

ትክክለኛ ያልሆነ ሕግ የተባለው የአላባማ ሕዝብ ብዙሀኑ ጥቁር ሆኖ ሳለ ምርጫ ውስጥ እንዳይገባ ተከልክሎ፣ጥቂት ነጮች ተሰባስበው ያወጡትን ሕግ በጥቁሮቹ ላይ የጫኑትን ነው።

ትክክለኛ ሕጎች በሌሉበት ሁኔታ ሕግ አክባሪ ሆኖ መገኘት፣አይምሮውን ማሠራት ተሥኖት፣ባርነትን የመረጠ ነው።። ትናንት የትህነግ፣ዛሬ የኦነግ ፖሊሲ ማሥፈፀሚያ “ሕጎች” <u>ትክክለኛ ያልሆኑ</u> ሕጎች እንደሆኑ እየታወቀ፣ለተግባራዊነታቸው ለሰውበላው ሥርዓት ቀጣይነት ተባባሪ መሆን ማለት በአማራው ላይ ወንጀል መፈፀም ነው፡

<u>የጥቁር አሜሪካኖች የሰላማዊ ትግል ዘዴዎች</u>

ጥቁር አሜሪካውያን ለዘመናት ይደርስባቸው የነበረውን የዘር ጭቆና ለመከላከል የታጠቀ ኃይል ባይኖራቸውም፣ጭቆናን ለመታገል የሰላማዊውን የትግል መንገድ በሰፊው ተጠቅመውበታል።

ትግሉ የተቀሰቀሰው እ አ አ ታህሳስ 1ቀን 1955ዓም ነው።ይህ የሰላማዊ ትግል እንዴት ተጀመረ?

በዚህ ቀንና ዓመተምህረት <u>ሮዛ ፓርከስ</u> የተባለች ጥቁር የልብስ ሥፌት ባለሙያ! ሥራ ውላ ሥትመለስ በጣም ደክሟት ሥለነበር ለጥቁሮች ከተከለከለው የነጮች አውቶቡስ ወንበር ላይ ትቀመጣለች።የነጭ ተሳፋሪዎች ሲገቡ ፣ሾፌሩ ለሮዛ ወንበሩን ለነጮች እንድትለቅ ያዛታል።ሮዛ ግን ንቅንቅ አልልም አለች።አውቶቡሱ ቆሞ፣ፖሊስ መጥቶ “ሕግ በመጣስ” በሚል ሮዛን ያስራታል።

በሮዛ መታሰር የሞንቶግሞሪ ጥቁር ሕዝብ ሆ ብሎ ይነሳል።ይህ ሕዝብ እንደዛሬው የነፍስ ወከፍ የመኪና ንብረትነት በጥቁር አሜሪካውያን ዘንድ ባልተስፋፋበት ወቅት ቁርጥ ውሳኔ አድርጎ ከታህሳስ 5ቀን 1955ዓም እስከ ህዳር 14ቀን 1956ዓም ድረስ በአውቶቡስ መጓዝን

ያቆማል።አብዛኛው በከፍተና ሙቀትና የአየር መለዋወጥ ሳይበገር ሥራ መመላለስን ሲመርጥ፣ሌላው መኪና በመጋራትና በሌላ ዘዴ ለአንድ ዓመት ያህል አድማውን ይቀጥላል።በዚህ ጊዜ ነው ቄስ ማርቲን ሉተር ኪንግም በትግሉ መድረክ ብቅ ያለው።

ይህ ቆራጥ የጥቁር አሜሪካውያን የኢኮኖሚ ማዕቀብ እርምጃ የአውቶቡስ ኩባንኛውን ከማክሰሩም አልፎ፣ለጥቁሮች መብት ከፍተኛ ውጤት ለማስገኘት መነሻ ሆኗል።ቀጥሎም ዘረኛ ህጎችን በመጣስ በሥራ ቦታዎች፣በሆቴሎችና ምግብ ቤቶች በራፍ ወዘተ በመሰለፍና በመኮልኮል ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል።

በዚህ ውሳኔ ድህው፣በዕድሜ የገፉ አዛውንት፣ሕፃናት ፣የጤና መታወክ የደረሰባቸው ወዘተ ከፍተኛ ችግር ላይ እንደወደቁ ታይቷል።ሆኖም ያለመሥዋዕትነት ሥርዓት ቀይሮ ሥርዓት መትከል አይቻልምና በዓላማ ፀንተው በመታገላቸው ሥርዓቱን አሥገድደው ሊያሥለውጡት በቅተዋል።

የአላባማ ክርስቲያኖች ንቅናቄና የሰብዓዊ መብት መሪ  ፍሬድ፣በበርሚንግሃም ከተማ በሚገኙት ምግብ ቤቶች፣ ሱቆች ወዘተ፣ጥቁሮችን የሚያንቋሽሹ ምልክቶች እንዲነሱ ከነጋዴዎች ጋር ሥምምነት ተፈጥሮ ማንሳት ቢጀመርም፣እንደገና መልሰው ሠቀሉት።ሥለዚህ የኢኮኖሚ ማዕቀብ ማድረግ ግድ ብሏል።በደቡብ አፍሪካም ተመሳሳይ ትግል ተካሂዶ፣ፈጣን ውጤት አሥገኝቷል።

በኢትዮጵያችንም ከትጥቅ ትግሉ ጎን ለጎን የኢኮኖሚ ማዕቀብን ያካተተ ሰላማዊ ትግል መጀመር አለበት።

አማራው ድል ያደርጋል!

አያሌው ፈንቴ